በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ
# ክፍል ስምንት

## መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

3. ሳያስመርሩ መውደድ ወይም ማፍቀር

- አንዳንድ ወላጆች ለልጆቻቸው ፍጹም ግትር ወይም መራር ሆነው ይገኛሉ፡፡ አንዳንድ ‹‹በትርና ተግሣጽ ጥበብን ይሰጣሉ ያልተቀጣ ብላቴና ግን እናቱን ያሳፍራል፡፡ … ልጅህን ቅጣ ዕረፍትንም ይሰጥሃል ለነፍስህም ተድላን ይሰጣታል፡፡›› _ምሳ 29፡15፣17፡፡_ እና ‹‹በበትር ከመምታት የሚራራ ሰው ልጁን ይጠላል ልጁን የሚወድድ ግን ተግቶ ይገሥጻዋል፡፡›› _ምሳ 13፡24፡፡_ የመሰሉ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃላትም ትርጉም በአግባብ ሳይረዱ ለመጠቀም ሲሞክሩ ሌሎቹን የመጽሐፍ ቃላት በመዘንጋት ነው፡፡
- ‹‹በትር›› የሚለው ቃል ጥሬ ቃሉ መወሰድ የለበትም ምክንያቱም ትርጉሙ፡-
  - *የተስተካከለ እይታ፡-* ልጆችን በንቃት የወላጆቻቸውን ቃል እንዲሰሙ ያደርጋል፡፡ ይህም ከስድብና ከመደብደብ ይልቅ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ነው፡፡
  - *ጽኑ አመለካከት፡-* በጸጥተኝነት ላይ የፈለጉትን ሳይሆን የሚጠቅማቸውን እየሰጡ ማሳደግ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በጨዋታ ቀናት የምንሰጠውን ገንዘብ ወይም ስጦታ በመከልከል የሠሩትን ጥፋት እንዲረዱ ማድረግና መሻሻል ሲያሳዩም ቅጣቱን በመተው አቃንቶ ማሳደግን ይመለከታል፡፡
- ስለዚህ ልጆቻችንን ከመገሰጻችን ወይም ከመቅጣታችን በፊት ለሚከተሉት ነገሮች ቅድሚያ እንስጥ፡-
  - ከመቆንጠጥ ወይም ከመምታታችን በፊት ወደ ልጆቹ ቀጥ ያለ አቀራረብ ይኑረን፡፡ ምክንያቱም ዱላውንም ቁንጥጫውንም ለምደው ቅጣታችን ውጤታማ ሳይሆን ሊቀር ይችላልና፡፡ ልጆቻችን እንዲወዱን ካላደረግናቸው ከእኛ ጋር በሚኖራቸው ግኑኝነት ፍርሐት ያደረባቸው ይሆናሉ፡፡ ይህም ፊት ለፊት ስንገናኝ ብቻ የሚያከብሩንና የሚፈሩን እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

3. ሳያስመርሩ መውደድ ወይም ማፍቀር…

- ልጆቻችንን ስንቀጣ ለልጆቻችን ያለንን ፍቅር እንዳያጠፋብን ክፉ ቃላቶችን ከጩኸት ጋር ከመጠቀም እንቆጠብ፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹በሰነፎች መካከል ከሚጮኽ ከገዢው ጩኸት ይልቅ የጠቢባን ቃል በጸጥታ ትሰማለች፡፡›› *መክ 9፡17፡፡* በማለት እንዳስተማረን ክፉ ቃል ልጆችን መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ሊያጠፋና ሥነ-ልቦናዊ ጉዳትም ሊያስከትልባቸው ይችላል፡፡ ይህን ዓይነት ያልተስተካከለ አካሄድ ወይም አሠራር በልጆቻችን ፊት መናቅን እንዳያስከትልብን እንጠንቀቅ፡፡
- ስህተት ተፈጽሞ በተመለከትንበት ጊዜ ከመቅጣት እንቆጠብ፡፡ ምክንያቱም ስንናደድ ቁጣችንን መቆጣጠር ስለማንችል፣ ልጆችም ተመሳሳይ ምላሽ ሊሰጡን እንዲችሉ ስለሚያደርግና እንዲሁም ቁጣችንንና ቅጣታችንን ለመቀበል በሚያስችላቸው መንፈሳዊና ሥ-ልቦናዊ መረጋጋት ውስጥ እንዳይገኙ ስለሚያደርጋቸው ነው፡፡ ስለዚህ ከሥራ ወደ ቤታችን ስንመለስ በቂ እረፍት አድርገን እስክንረጋጋ ድረስ ክሶችንና ችግሮችን ከመስማት እንቆጠብ፡፡ እንደዚሁ ሁሉ ሚስቶችም ከባሎቻቸው ጋር በችግሮች ዙሪያ ለመወያየት የሚያስችላቸውን ትክክለኛ ጊዜ መምረጥ ይኖርባቸዋል፡፡
- ልጆቻችንን ስንቀጣ ለራሳችን ሳይሆን ልጆቻችንን ስህተት ለመሥራት ላበቃቸውን ተፈጥሮአቸው፣ አስተሳሰባቸውና እንዲሁም አስተዋጽኦ ላደረጉ ክስተቶች ትኩረት እንስጥ፡፡
- ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹ተስፋ ገና ሳለች ልጅህን ገሥጽ፥ መሞቱንም አትሻ፡፡›› *ምሳ 19፡18፡፡* በማለት የተናገረውን ዘወትር ልብ አንበል፡፡ ልጆቻችን በሠሩት ስህተት ላይም ችክ ከማለት ይልቅ እግዚአብሔር ለእኛም ሆነ ለልጆቻችን የሚሻለውን ሁሉ እንደሚያደርግልን እንወቅ፡፡ ስለዚህ መንፈሳዊው ሕይወታቸውን እንዳናጠፋና ሥነ ልቦናቸውንም እንዳንጎዳ እንጠንቀቅላቸው፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

**ልጆችን ማስመረር የሚከተሉትን ያስከትላል…**

- ልጆችን ከፍርሐት የተነሣ በሚያስቡት ሁሉ ከራሳቸው ጋር ትግል የሚገጥሙ ይሆናሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ልጆችም ከቅጣት የተነሣ ማንኛውንም ነገር ለመሥራት ይፈራሉ፡፡
- ልጆች ከወላጆቻቸው እይታ ለመሸሸግ ሲሉ ውሸታምና አታላይ ይሆናሉ፡፡ በዚህ ሲገኙም የበለጠ አታላይና ጥፋታቸውን ለመሰወር በርካታ የጥፋት መንገዶችን የሚከተሉ ይሆናሉ፡፡
- ከሌሎች ሰዎች ጋር ከእንስሳትና ከአእዋፋት ጋር ሳይቀር ኃይልን የሚጠቀሙ የሚነኩትን ዕቃ ሁሉ የሚሰብሩ ቁጡ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ከሥራ ባልደረቦቻቸው፣ ከወላጆቻቸውና ወደፊትም ከልጆቻቸውም ጋር ሳይቀር ባላቸው ግኑኝነት መራር ይሆናሉ፡፡ የዚህም ችግር ምንጩ በልጅነታቸው ያለፉበት የሚያስመርር ሕይወት ስሜታቸውን መጉዳቱ ሲሆን ይህም የሌሎችን ጉዳትና ምሬት የማይረዱ እስከመሆን ያደርሳቸዋል፡፡
- መራርነት ከቤቱ ውጪ በጎን የሚሻ ሰውንም እስከመጉዳት ይደርሳል፡፡ ይህም ሰው ፍላጎቱን ለማሟላት ኦርቶዶክሳውያን ካልሆኑት ጋር ግኑኝነትን ይመሠርታል፡፡ ይህም ከእምነት ወደ ክህደት የሚደረግ ጉዞ የልጆችን ሕይወት ጨርሶ እንደማጥፋት ይቆጠራል፡፡
- መራርነት የሚጀምረው ልጆችን ሳናመሰግንና ሳናበረታታ ትእዛዝ ብቻ የምንሰጥ ከመሆን ነው፡፡ ይህም የምንናገረውና የምንሠራው እየተጋጨ ልጆችን ወደ ባሰ ግራ መጋባት ያመራቸዋል፡፡ በዚህም የተነሣ ልጆች ነውጠኞች ብሎም በደካማነታቸው ምክንያት በሌሎች ዘንድ መናቅን ያስከትልባቸዋል፡፡
- ወላጆች ሆይ! ልጆቻችን መላ ሕይወታቸውን ከእኛ ጋር እንዲጣበቁ መፈለግ ስህተት እንደሆነ እንረዳ፡፡ የበሰለ የወይን ፍሬ ከዛፉ ካልተቆረጠ ይበሰብሳል፡፡ ብዙ ፍሬ እንዲያፈራም ከተፈለገ መቁረጥ(መግረዝ)፣ ፍሬውንም በምድር መዝራት ይገባል፡፡ ይህም አዲስ ዛፍ ሆኖ አዲስ ፍሬ ለማፍራት ያበቃዋል፡፡ እንዲሁ የልጆቻችንን ማንነት ከልጅነት አንስቶ ለጋብቻም ብቁ እንኪሆኑ ተገቢ በሆነ አስተዳደግ በአግባብ መገንባትና መርዳት ያስፈልጋል፡፡

# በቤታችን ያለች ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ ምልክቶች

## 4. የበላይነት የሌለበት ፍቅር

- አንዳንድ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር ልጆቻቸውን አእምሮ የጎደላቸው፣ ሐሳብ ማመንጨት የማይችሉ መልካም ስብዕናም የሌላቸው አድርገው በማሰብ ራሳቸውን እንደ ልዕለ ኃያል በመቁጠር ይነጋገራሉ። ይህም በሚከተሉት መንገዶች ይገለጣል፡-
  - ደጋግሞ መመሪያ በመስጠት።
  - የሚናገሩትን ራሳቸው ለመፈጸም ሳይሞክሩ ዝም ብሎ ደጋግሞ መመሪያ መስጠት።
  - ልጆችን በሚያሸማቅቅ መልኩ በሌሎች ፊት ለልጆች መመሪያ መስጠት።
  - ወላጆች ለጉዳዩ የሚመጥኑ ቢሆኑም ባይሆኑም ወይም ጉዳዩ የማያስፈልግ/የሚያስፈልግ ቢሆንም/ባይሆንም መመሪያ ወይም ትእዘዝን ዝም ብሎ ማስተላለፍ።
  - ለ21ኛው መቶ ክፍለዘምን የሚመጥን ቢሆንም ባይሆንም ዝም ብሎ ትእዛዝ/መመሪያ መስጠት።
  - የልጆችን ዕድሜ ባላገናዘበ መልኩ ለዕድሜያቸው ባይመጥንም መመሪያ/ትእዛዝ ማስተላለፍ።
- እነዚህ የተገለጹት ሁሉ ልጆች በወላጆቻቸው ላይ አመጸኞች እንዲሆኑና መታዘዛቸውም ከፍቅርና ከመረዳት የተነሳ ሳይሆን ከደካማነታቸውና ከተበላሸው ማንነታቸው የተነሳ የሚገለጥ ለመሆን ይበቃል።
- ሌላው የወላጆች ልዕለ ኃያልነት የሚገለጥበት መንገድ ወላጆች ለልጆቻቸው ምኞት፣ ስሜትና ፍላጎት ትኩረት በመንፈግ የራሳቸውን ፍላጎት በሚያስፈጽሙበት ሁኔታ ውስጥ ነው።
- ይህም አካሄድ ለምሳሌ እናት ለሴት ልጆዋ እናት የመረጠችላትን ብቻ እንድታገባ በማስገደድ፣ አባትም ልጁ ያለፍላጎቱና ዝንባሌው አባት የመረጠውን ትምህርት/ሞያ እንዲያጠና በማስገደድ ይገለጣል። ይህ ጣልቃ ገብነትም ልጆቻቸው ካገቡ በኋላም ስለሚቀጥል በልጆቻው ትዳር ላይ ከፍ ያለ ቀውስን ያስከትላል።
- ወላጆች ሆይ! ልጆቻችንን የተመጣጠነና፣ በቂ ተዋጽዖ ያለው አስተዳደግ እንዲኖራቸው፣ የእኛ ግልባጭ ሳይሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች የተዋጣላቸውም ኦርቶዶክሳውያን አድርገን፣ ያላግባብም ጣልቃ ሳንገባባቸው እናሳድጋቸው።

# ይቆየን።

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org